BRITISH COUNCIL #EastAfricaArts

**ኒው አርት ኒው ኦዲየንስስ (nAnA) 2018**

**ለአመልካቾች የሚጠቅሙ መረጃዎች**

ርዕስ ማውጫ፡-


ገጽ 2 | nAnA 2018 ቁልፍ መረጃና ተቀባይነት ማግኘት

ገጽ 3 | የምርጫ መመዘኛ፣ ሂደቱና ፕሮግራም

ገጽ 4 – 6 | ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

## ኒው አርት ኒው ኦዲየንስስ (nAnA) 2018:

*ኒው አርት ኒው ኦዲየንስስ* (nAnA) እንግሊዝ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሰሜን አየርላንድ፣ ሩዋንዳ፣ ስኮትላንድ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ ታንዛንያ፣ ዩጋንዳ እና ዌልስ ውስጥ በሚገኙ ከተሞች ለሚኖሩ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 35 ዓመት ለሚሆኑ የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ የሥነ ጥበብ ድርጅቶችና የሥነ ጥበብ ማኅበራት የሚቀርብ ዓመታዊ ግብዣ ነው። nAnA ከእነዚህ ከተሞች ውስጥ የተውጣጡ የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች በጋራ ሆነው አዲስ የሥነ ጥበብ ሥራ የሚያዘጋጁበት እንዲሁም ሥራቸውን በእነዚህ አገሮች ውስጥ ለሚገኙ ታዳሚዎች የሚያቀርቡበት አጋጣሚ ይሰጣቸዋል።

**nAnA 2018ን የሚመለከቱ ቁልፍ መረጃዎች:-**

1. nAnA በ2018 ለ5 አዳዲስ ፕሮጀክቶች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፤
2. ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት እስከ 30,000 ፓውንድ ድረስ ገንዘብ ይመደባል፤
3. ከተጠቀሱት አገሮች (**ከላይ ተዘርዝረዋል**) የተውጣጡ የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ የሥነ ጥበብ ድርጅቶች እና/ወይም የሥነ ጥበብ ማኅበራት አዲስ የሥነ ጥበብ ሥራ በጋራ መፍጠር፣ በጋራ ማመቻቸት ወይም በጋራ ማዘጋጀት እንዲችሉ መገናኘት ይኖርባቸዋል። ይህን ብቃት በተመለከተ ማብራሪያ የያዙ ምሳሌዎች ገጽ 4 ላይ ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች በሚለው ስር ማግኘት ይቻላል፤
4. nAnA 2018 ቀደም ሲል ከሌሎች አገሮች ጋር በመስኩ የመደጋገፍና ትስስር የመፍጠር ሥራ ያከናወኑ እንዲሁም ያንን ማሳደግ የሚፈልጉ የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ የሥነ ጥበብ ድርጅቶች እና/ወይም የሥነ ጥበብ ማኅበራት ለያዟቸው ፕሮጀክቶች ድጋፍ ለማድረግ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። አብረው የሚሠሩ አዳዲስ ቡድኖች መፈጠራቸው የሚበረታታ ሲሆን ብዙ ጊዜ በሚነሱ ጥያቄዎች ክፍል ላይ ብሪቲሽ ካውንስል በሥነ ጥበብ መስክ አብረው የሚሠሩ ወገኖችን ዩናይትድ ኪንግደም እና ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ለማግኘት ምን ዓይነት ድጋፍ እንደሚሰጥ ማየት ይቻላል፤
5. በሥነ ጥበብ ሥራዎቹ ይዘትም ሆነ በጭብጦቹ ላይ ምንም ዓይነት የምርጫ ገደብ አልተደረገም።

**ለnAnA 2018 ብቃቱን የሚያሟሉ:-**

1. አመልካች የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች በግለሰብ፣ በድርጅት ወይም በማኅበር ደረጃ ማመልከት ይችላሉ፤
2. እያንዳንዱ ፕሮጀክት አዲስ የፈጠራ ሥራ በማዘጋጀት ወይም በአዲስ የሥነ ጥበብ ዘርፍ ላይ ማተኮር ይኖርበታል፤
3. በአንድ ፕሮጀክት ላይ ቢያንስ **ሦስት** አገሮች መሳተፍ የሚኖርባቸው ሲሆን ከእነዚህ አገሮች ውስጥ ቢያንስ **ሁለቱ** ከምሥራቅ አፍሪካ (እና ከላይ ከተጠቀሱት አገሮች ውስጥ) መሆን ይኖርባቸዋል፤
4. nAnA ድጋፍ ለመስጠት ትኩረት የሚያደርገው በተጠቀሱት አገሮች ውስጥ በሚገኙ **ከተሞች** ውስጥ ላሉ የሥነ ጥበብ ዘርፎች ነው - የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ የሥነ ጥበብ ሥራዎቹና ታዳሚዎች ከከተሞች ጋር ግንኙነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፤
5. እያንዳንዱ ፕሮጀክት ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 35 የሆናቸውን በግንባር ለማግኘት፣ ታዳሚዎችን ደግሞ በኢንተርኔት ለማግኘት ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል። nAnA ከምሥራቅ አፍሪካና ከዩናይትድ ኪንግደም የተገኙ አዳዲስ የዘመኑ የሥነ ጥበብ ሥራዎች በሰፊው እንዲታዩና በሰፊው እንዲታወቁ የማድረግ ዓላማ አለው። በመሆኑም ፕሮግራሙን ከሚከታተሉ ሰዎች ጋር በኢንተርኔት እና/ወይም በግንባር መገናኘት ወሳኝ ጉዳይ ነው፤
6. በፕሮጀክቱ የሚሳተፉ ቁልፍ ባለድርሻዎች በሙሉ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 35 መሆን ይኖርበታል፤
7. ፕሮጀክቶቹ በሌሎች ገንዘብ ለጋሽ አጋሮችም ድጋፍ ሊደረግላቸው ይችላል፤
8. አመልካቾች *ለኒው አርት ኒው ኦዲየንስ* ከአንድ ጊዜ በላይ ማመልከት ይችላሉ፤
9. የnAnA 2016/17 የገንዘብ ድጋፍ አግኝተው የነበሩ (*የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ አጋሮች*) ለnAnA 2018ም ማመልከት ይችላሉ። ይሁንና የnAnA 2016/17 *የመጀመሪያ ደረጃ አጋር* የነበረ ለnAnA 2018 ቀዳሚ አጋር ሆኖ ማመልከት **አይችልም**፤
10. ሁሉም ፕሮጀክቶች ከብሪቲሽ ካውንስል የገንዘብ ድጋፍ ባገኙ በ12 ወር ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል፤
11. ክፍያ ለማግኘት የአጋማሽ ፕሮጀክት ሪፖርትና የመደምደሚያ ፕሮጀክት ሪፖርት እንዲቀርብ ይፈለጋል፤ እነዚህ ሪፖርቶች የሚቀርቡበት ቅፅ ይላካል፤
12. ፕሮጀክቱን በበላይነት የሚቆጣጠረው አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት መሆን አለበት። የገንዘብ ድጋፉን ለማግኘት የባንክ ሒሳብና የቀበሌ መታወቂያ ሊኖራቸው ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ የፕሮጀክቱ አጋማሽና መደምደሚያ ላይ ሪፖርቶች የማቅረብ እንዲሁም ፕሮጀክቱን በተመለከተ ከውጭ አካላት ጋር ግንኙነት የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፤
13. ከብሪቲሽ ካውንስ ጋር ውል በሚፈረምበት ጊዜ 70% የገንዘብ ድጎማ የሚለቀቅ ሲሆን የቀረው 30% በጀት የሚለቀቀው የፕሮጀክቱን አጋማሽ ሪፖርት ሲያቀርቡ ነው።

**የ2016/17 nAnA ፕሮጀክቶችን በሚከተለው ሊንክ ማየት ይችላሉ:-** https://www.britishcouncil.org/east-africa-arts/projects/nana

**የ nAnA 2018 የምርጫ መስፈርት፡-**

ማመልከቻዎቹ በሚመዘኑበት ጊዜ ምርጫውንና ቃለ ምልልሱን የሚያካሂደው ቡድን የሚከተሉትን 5 ጥያቄዎች ይጠይቃል፡-

1. ይህ ፕሮጀክት አስደሳች፣ የፈጠራ ችሎታ የሚንጸባረቅበትና ወቅታዊ የሆነ **አዲስ የሥነ ጥበብ ሥራ** ለማቅረብ ያቀደ ነው?
2. ይህ አዲስ የሥነ ጥበብ ሥራ እየተሠራ ያለው እና/ወይም የሚቀርበው በተጠቀሱት አገሮች ውስጥ በሚገኙ የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ የሥነ ጥበብ ድርጅቶች እና/ወይም የሥነ ጥበብ ማኅበራት መካከል ባለ **ጠንካራ ትስስር** አማካኝነት ነው?
3. ይህ አዲስ የሥነ ጥበብ ሥራ በዩናይትድ ኪንግደምና በምሥራቅ አፍሪካ ለሚገኙ በኢንተርኔትና በግንባር ለሚከታተሉ አዳዲስ **ታዳሚዎች** የሚቀርበው እንዴት ነው? የሥነ ጥበብ ሥራውን የሚከታተሉት ታዳሚዎች ብዛት ምን ይህል ነው? ምን ያህል ታዳሚዎች እንደሚገኙ ይጠበቃል? የሚጠበቁት ሰዎች ብዛትስ እውነታውን ያገናዘበ ነው?
4. በፕሮጀክቱ ውስጥ ቁልፍ ድርሻ ያላቸው (አስተዳዳሪዎች፣ አዘጋጆች፣ የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ አደራጆች፣ ሥራ አስኪያጆችና አመልካቹ) ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 35 ዓመት ነው? የፕሮጀክቶቹ ታዳሚዎችስ በአመዛኙ **ከ18 እስከ 35 ባለው የዕድሜ ክልል** ውስጥ የሚገኙ ናቸው?
5. **ባጀቱ** ምን ምን ላይ እንደሚውል በግልጽ የሚታወቅ፣ በሚገባ የተጠናና እውነታውን ያገናዘበ ነው?

**የnAnA 2018 የምርጫ ሂደት፡-**

ለነው አርት ነው አፊየንሰስ ለማመልከት ኢንተርኔት ላይ የሚገኘውን የማመልከቻ ቅጽ መሙላት ይጠበቅብዎታል፤ ማመልከቻው በዚህ አድራሻ ይገኛል፡- https://www.britishcouncil.org/east-africa-arts/opportunities

ኢንተርኔት ላይ የሚገኘው ማመልከቻ በፕሮጀክቱ ላይ ምን ማድረግ እንዳሰቡ የሚጠይቁ **5 ጥያቄዎችን** ይዟል፤ ከተጠቀሱት አገሮች፣ ከተሞችና አብረዎት ከሚሠሩት ጋር ስላለዎት ግንኙነትና ተደጋግፋችሁ ስለምትሠሩበት መንገድ፣ ለምን ያህል ታዳሚዎች እንደምታቀርቡ፣ ያወጣችሁት ፕሮግራምና መረጃ የምትለዋወጡበት መንገድ እንዲሁም ባጀታችሁን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ይነሳሉ። ከዚህም ሌላ ማካተት የሚፈልጓቸውን ምስሎች፣ ቪዲዮዎችና ሌሎች የማጠናከሪያ መረጃዎችን ማገናኘት የሚችሉበት አጋጣሚም ይኖራል።

ማመልከቻ ሲያስገቡ እኛ ጋር መድረሱን የሚያረጋግጥ ኢሜይል ይደርስዎታል። ከዚያም ሰኞ፣ ነሐሴ 13 ላይ ፕሮጀክትዎት ተመርጦ ከሆነ ይነገርዎታል። **ማሳሰቢያ፡- ፕሮጀክትዎት ከተመረጡት መካከል የሚገኝ ካልሆነ ምንም ዓይነት መልእክት አይደርስዎትም።** ምርጫውን የሚያካሂዱት የnAnA የገንዘብ ድጎማ በሚሰጥባቸው በእያንዳንዳቸው አገሮች ውስጥ በሚገኙ የብሪቲሽ ካውንስል የሥነ ጥበብ ሥራ አስኪያጆች ነው።

ፕሮጀክትዎት ከተመረጠ በስካይፒ በሚካሄድ ቃለ ምልልስ ላይ እንዲሳተፉ የሚጋበዙ ሲሆን ይህ **ከ45 ደቂቃ እስከ 1 ሰዓት** ይፈጃል። ከላይ በተጠቀሱት 5 ጥያቄዎች ላይ ትኩረት በማድረግ በማመልከቻዎት ላይ ማብራሪያ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ።

ያልተሳካላቸው ለምርጫ የቀረቡ አመልካቾች በሙሉ **ጥያቄ ካቀረቡ** ማመልከቻቸውን በተመለከተ ገንቢ አስተያየት ይሰጣቸዋል።

**በ nAnA 2018 የምርጫ የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮች፡-**

- የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ የሚጀመረው፡- **ሰኞ ሰኔ 4 (እ. ኤ. አ.)፤**
- ማመልከቻ ማስገባት የሚያበቃበት ዕለት፡- **እሁድ ሐምሌ 15፣ በዩናይትድ ኪንግደም የሰዓት አቆጣጠር እኩለ ሌሊት ላይ፤**
- ምርጫ የሚካሄደው፡- **ከሰኞ ሐምሌ 16 - እሁድ ነሃሴ 12 (እ. ኤ. አ.)፤**
- ተመራጮች እጩ እንደሆኑ የሚነገራቸውና ለቃለ ምልልስ የሚጋበዙት፡- **ሰኞ ነሃሴ 13 (እ. ኤ. አ.)፤**
- ከተመረጡ አመልካቾች ጋር በስካይፒ ቃለ ምልልስ የሚደረግበት ጊዜ፡- **ከሰኞ 27 ነሃሴ - አርብ 31 ነሃሴ (እ. ኤ. አ.)፤**
- የመጨረሻ ምርጫ የሚደረግበት ቀን፡- **አርብ መስከረም 14 (እ. ኤ. አ.)፤**
- ሁሉም አመልካቾች መረጃ የሚያገኙበት ቀን፡- **ሰኞ መስከረም 17 (እ. ኤ. አ.)፤**
- ለፕሮጀክቶች ክፍያ የሚፈፀምበት ቀን፡- **መስከረም/ጥቅምት 2018 (እ. ኤ. አ.)፤**
- ፕሮጀክቶች የሚጀመሩበት ቀን፡- **ኅዳር 1 ቀን 2018 (እ. ኤ. አ.)።**

BRITISH COUNCIL #EastAfricaArts

***ኒው አርት ኒው ኦዲየንስስ (nAnA) | ብዙ ጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች***

ለመጨረሻ ጊዜ ማስተካከያ የተደረገበት፡- ግንቦት 8 ቀን 2018 (እ. ኤ. አ.)

**እዚህ ደረጃ ላይ ደርሼ አብረውኝ የሚሠሩት እነማን እንደሆኑ ባላውቅስ?**

አመልካቾች *ኒው አርት ኒው ኦዲየንስስ* ላይ ለማቅረብ ያሰቡትን ነገር ከማስረከባቸው በፊት ከተጠቀሱት አገሮች ውስጥ ከእነማን ጋር አብረው መሥራት እንደሚፈልጉ ጥናትና ምርጫ አድርገው እንዲመጡ ይጠበቅባቸዋል። የብሪቲሽ ካውንስል የምሥራቅ አፍሪካ ፕሮግራም አንኳር ዓላማ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 35 ዓመት በሆነ የፈጠራ ችሎታ ባላቸው ምሥራቅ አፍሪካውያንና ብሪታንያውያን መካከል ግንኙነት መፍጠር ነው። አብረዎት ሊሠሩ የሚችሉ የፈጠራ ችሎታ ያላቸውንና አጋር የሚሆኑዎትን ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት ያግዝ ዘንድ፣ በምሥራቅ አፍሪካና በዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ በርካታ አስደናቂ የፈጠራ ሥራ ፕሮጀክቶችን እየሠሩ ያሉትን የሚከተሉትን የብሪቲሽ ካውንስል ድረ ገጾች ስናቀርብልዎት ደስ ይለናል።

***ምሥራቅ አፍሪካን እና ዩናይት ኪንግደምን በሚመለከት፡-***

የምሥራቅ አፍሪካ ሥነ ጥበብ ማይክሮሳይት፡- www.britishcouncil.org/east-africa-arts

የምሥራቅ አፍሪካ ሥነ ጥበብ ኢንስታግራም ገጽ፡- www.instagram.com/eastafricaarts

***የዩናይትድ ኪንግደምን የሥነ ጥበብ ሥራዎች በሚመለከት፡-:***

የሚታዩ የሥነ ጥበብ ሥራዎች፡- http://visualarts.britishcouncil.org

ሥነ ሕንጻ፣ ንድፍ እና ፋሽን፡- http://design.britishcouncil.org

ሥነ ጽሑፍ፡- https://literature.britishcouncil.org

ተውኔት እና ውዝዋዜ፡- https://theatreanddance.britishcouncil.org

ሙዚቃ፡- http://music.britishcouncil.org

ፊልም፡- http://film.britishcouncil.org

***ዘርፈ ብዙ የሥነ ጥበብ ሥራ ዓይነቶች፡-***

የሥነ ጥበብ እና ዲጂታል ሥራዎች፡- https://medium.com/intersections-arts-and-digital-culture-in-the-uk

የፈጠራ ምጣኔ ሃብት፡-http://creativeconomy.britishcouncil.org

ባህላዊ ክህሎቶች፡- https://www.britishcouncil.org/cultural-skills-unit

ባህል እና መሻሻል፡- https://www.britishcouncil.org/arts/culture-development

የፈጠራ ሥራ ማእከላት፡- http://creativeconomy.britishcouncil.org/projects/hubs/

ብሪቲሽ ካውንስል የሥነ ጥበብ ሥራዎች ገጽ፡- https://www.britishcouncil.org/arts

***ማሳሰቢያ፡- ለሁሉም አመልካቾች ወጥነት ያለው መረጃ ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ብሪቲሽ ካውንስል ይህ ኒው አርት ኒው ኦዲየንስስ በሚካሄድበት ወቅት ወይም ለሁሉም ክፍት የሆነውን ግብዣ በሚያቀርብበት ወቅት አመልካቾችን በቀጥታ ከአጋሮች ጋር ማገናኘት አይችልም።***

**ዕድሜዬ ከ18 – 35 መሆን ያለበት ለምንድን ነው?**

የምሥራቅ አፍሪካው የብሪቲሽ ካውንስል የሥነ ጥበብ ፕሮግራም በተቀዳሚነት፣ በዩናይትድ ኪንግደምና በምሥራቅ አፍሪካ በሚገኙ ወጣት የፈጠራ ሥራ ባለሙያዎች መካከል ግንኙነት የመፍጠር ስትራቴጂ አለው፡- http://bit.ly/2gV6rFz. ይህ ሁልጊዜ ሊሳካ እንደማይችል ስለምንገነዘብ የፕሮጀክቱ ዋና አመልካቾች፣ ተሳታፊዎችና ታዳሚዎች የሚቻል ከሆነ ከ18-35 ዓመት የሆናቸው እንዲሆኑ ይፈለጋል።

ብሪቲሽ ካውንስል ውስጥ ማመልከቻ ማቅረብ የሚችሉባቸው በርካታ ዓለም አቀፍ አጋጣሚዎች አሉ፤ እዚህ ላይ ይመልከቱ፡- https://www.britishcouncil.org/arts/opportunities

***ነው አርት ነው ኦዲየንስስ* የገንዘብ ድጋፍ የማያደርግባቸው መስኮች ምንድን ናቸው?**

- ለትምህርታዊ ስብሰባዎች፣ ለረዥም ስብሰባዎችና ለትንንሽ ስብሰባዎች፡- ለአዲስ የሥነ ጥበብ ፈጠራ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ካልሆኑ በስተቀር፤
- *ነው አርት ነው ኦዲየንስስ* የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ ከመገኘቱ በፊት የተዘጋጀ የሥነ ጥበብ ሥራ፤
- አዳዲስ ታዳሚዎችን ለማግኘት ትኩረት የማይሰጡ ፕሮጀክቶች።

***ነው አርት* ስትሉ ምን ማለት ፈልጋችሁ ነው?**

ብሪቲሽ ካውንስል በስምንት ዓይነት የሥነ ጥበብ ሥራዎች ዙሪያ ይሠራል። እነዚህም ሥነ ሕንፃ፣ የፋሽን ንድፍ፣ ፊልም፣ ሙዚቃ፣ ውዝዋዜና ተውኔት፣ የፈጠራ ምጣኔ ሃብት፣ ባሕላዊ ክህሎቶች፣ ሥነ ጽሑፍ እንዲሁም የሚታዩ የሥነ ጥበብ ሥራዎች ናቸው።

*ነው አርት ነው ኦዲየንስስ* ከእነዚህ መካከል ወይም በእነዚህ ዙሪያ የሚዘጋጁ አዳዲስ የሥነ ጥበብ ሥራ ፕሮጀክቶችን ማግኘት ይፈልጋል። ከዚህም ሌላ እነዚህን የሥነ ጥበብ መስኮች የሚቀናቀኑ ፕሮጀክቶችን ማግኘት እንፈልጋለን። ከዚህ በፊት የተዘጋጁ ሥራዎችን የማግኘት ፍላጎት የለንም።

**ለሁሉም ክፍት በሆነው *ነው አርት ነው ኦዲየንስስ* መሳተፍ የሚችሉት የትኞቹ አገሮች ናቸው?**

በ2018 የብሪቲሽ ካውንስል የምሥራቅ አፍሪካ የሥነ ጥበብ ፕሮግራም እና *ነው አርት ነው ኦዲየንስስ* ሥራውን የሚያካሂደው በእንግሊዝ፣ በኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በሰሜን አየርላንድ፣ በሩዋንዳ፣ በስኮትላንድ፣ በደቡብ ሱዳን፣ በሱዳን፣ በታንዛንያ፣ በዩጋንዳ እና በዌልስ ነው። ሥራችንን የምናካሂደው የብሪቲሽ ካውንስል ቢሮዎች በሚገኙባቸው አገሮች ውስጥና ለሥራው የሚያስፈልጉ ነገሮች ካሉ ነው።

**ማመልከቻ ለማቅረብ የተጠቀሱት አገሮች ዜጋ ወይም ነዋሪ መሆን ያስፈልገኛል?**

*የነው አርት ነው ኦዲየንስስ* **አመልካቾች** በእንግሊዝ፣ በኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በሰሜን አየርላንድ፣ በሩዋንዳ፣ በስኮትላንድ፣ በደቡብ ሱዳን፣ በሱዳን፣ በታንዛንያ፣ በዩጋንዳ እና በዌልስ የሚኖሩ መሆን አለባቸው። አመልካቾች ከእነዚህ አገሮች ውስጥ በአንዱ የመኖር ወይም የመሥራ መብት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። በፕሮጀክትዎት ላይ **የሚሳተፉት ሰዎችም** ከእነዚሁ አገሮች የተውጣጡ መሆን ይኖርባቸዋል። የፕሮግራሙ **ታዳሚዎችም** በዋነኝነት ከእነዚህ አገሮች የመጡ ሊሆኑ የሚገባ ቢሆንም ከየትኛውም የዓለም ክፍል የመጡ ሊሆኑም ይችላሉ።

***ነው ኦዲየንስስ* ሲባል ምን ማለት ነው?**

*የነው አርት ነው ኦዲየንስስ* አላማ፣ በዩናይትድ ኪንግደም የሚገኙ ታዳሚዎች አዳዲስ የምሥራቅ አፍሪካ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን እንዲመለከቱ ማስቻል እንዲሁም በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ ታዳሚዎች አዳዲስ የዩናይትድ ኪንግደምን ሥራዎች እንዲያዩ ማድረግ ነው። *ነው አርት ነው ኦዲየንስስ* የእርስዎን ሥራ አይተው የማያውቁ ዕድሜያቸው ከ18-35 ለሚሆን ታዳሚዎች የሚቀርቡ ፕሮጀክቶችን ይፈልጋል። ቀድሞውንም ያሉ ታዳሚዎችን ምንጊዜም በደስታ እንቀበላለን፤ ይሁን እንጂ ለ*ነው አርት ነው ኦዲየንስስ* በሚያቀርቡት የሥራ እቅድ ላይ የሥነ ጥበብ ሥራዎትን እንዴት ለአዳዲስ ታዳሚዎች እንደሚያቀርቡ መግለፅ ይኖርብዎታል።

**በግሌ ማመልከት እችላለሁ?**

ግለሰቦች የባንክ ሒሳብ፣ የቀበሌ መታወቂያ ካርድና ትላልቅ ፕሮጀክቶችን የመምራት ልምድ እንዳላቸው ማረጋገጥ እስከቻሉ ድረስ *ኒው አርት ኒው ኦዲየንሰስ* ማመልከቻዎቻቸውን ለመቀበል ዝግጁ ነው። በፕሮጀክቱ ውስጥ ቢያንስ **ሦስት** አገሮች መሳተፍ ያለባቸው ሲሆን ቢያንስ **ሁለቱ** የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች (እና በዚህ የማመልከቻ ሰነዶች ውስጥ ከተጠቀሱት አገሮች የመጡ) ሊሆኑ ይገባል።

**የመረጥኩት ፕሮጀክት መከናወን የሚኖርበት መቼ ነው?**

ሁሉም *የኒው አርት ኒው ኦዲየንሰስ* ፕሮጀክቶች ከብሪቲሽ ካውንስል የገንዘብ ድጋፍ ባገኙ በ12 ወር ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል።

**“የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ የሥነ ጥበብ ድርጅቶች እና/ወይም የሥነ ጥበብ ማኅበራት አዲስ የሥነ ጥበብ ሥራ አብረው ሆነው በጋራ ለመፍጠር፣ በጋራ ለማመቻቸት ወይም በጋራ ለማዘጋጀት መገናኘት ይኖርባቸዋል” ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው?**

አዳዲስ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን አብረን ልንሠራ የምንችልባቸው በርካታ አስደሳች አጋጣሚዎች አሉ። እንዲህ የመሰሉ ግንኙነቶችን እንዴት መመስረት እንደምንችል የሚያሳዩ ጥቂት ምሳሌዎች ከዚህ በታች ተገልፀዋል፡-

- አንድ **የሩዋንዳ የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች ቡድን በኬንያ** ከሚገኙ **የሚታዩ የሥነ ጥበብ ሥርዎችን** ከሚያቀርቡ የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር በመተባበር አዲስ የውዝዋዜ ዓይነት የፈጠረ ሲሆን የስኮትላንድ **የባሕል ዝግጅት አቅራቢ** ባደረገው ድጋፍ **በስኮትላንድ** በአንድ ዝግጅት ላይ ትርኢቱን አቅርቧል፤
- አንድ **ስኮትላንዳዊ** የዲጂታል **ሥነ ጥበብ ባለሙያ በዌልሽ፣ በዩጋንዳ** እና **በታንዛንያ** ከሚገኙ የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች ጋር በመተባበር አንድ አዲስ የሥነ ጥበብ ሥራ ፈጥሯል። ከዚያም ዕድሜያቸው ከ18-35 ለሆኑ **የብሪታንያ** እና **የምሥራቅ አፍሪካ** ታዳሚዎች የምሥራቅ አፍሪካ ዲጂታል የሥነ ጥበብ ሥራዎች መጽሔት **ባዘጋጀው የኢንተርኔት ፕሮግራም ላይ** ሥራው **ቀረበ፤**
- **ሱዳናዊው የድምጽ ባለሙያ ከሰሜን አይርላንዳዊው** እና **ከኬንያዊው የሥነ ጥበብ ባለሙያዎች** ጋር በመተባበር፣ **በዩጋንዳ** እና **በደቡብ ሱዳን** ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ በቀረበው ዝግጅት ላይ አዲስ የሥነ ጥበብ ሥራውን አቀረበ፤
- **በእንግሊዝ** የሚገኝ አንድ **የሥነ ጥበብ ድርጅት** በቢዬናሌ፣ **ታንዛኒያ** ውስጥ **ለሚቀርብ ትርኢት** የሚያስፈልግ አዲስ የሥነ ጥበብ ሥራ **ለማዘጋጀት በኢትዮጵያ** እና **በዩጋንዳ** ከሚገኙ **ፎቶግራፍ አንሺዎች** ጋር በመተባበር ይሠራል።